## እንግዶች እንኳን ደህና መጣችሁ!

**የልጅ በረከት**

ወንድማችን ሳሚና እህታችን ሙሉ በሁለተኛ ልጅ ተባርከዋል። ወላጆች እና ቤተሰቦች እንዲሁም ቤተ ክርሲቲያን እንኳን ደስ ያለን። ስለ ስጦታው እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን።

**የአርብ ፕሮግራም**

በአርብ **ፕሮግራም** እግዚአብሔር ግሩም የጸሎትና የትምህርት ጊዜ እየሰጠን ነው። በተለይም ደግሞ አሁን ወንድም ሲሳይ "የእግዚአብሔር መንግስት" በሚል ርእስ ተከታታይ ትምህርት በማስተማር ላይ ይገኛል። በዚህ የጸሎት ፕሮግራም ላይ በመገኘት በጸሎትና ቃሉን በመማር እንድንተጋ ቤተ ክርስቲያን ታሳስባለች። እንዲጸለይላችሁ የምትፈልጉ ወገኖችም መሪዎችን ማነጋገር ትችላላችሁ። ጌታ ይባርካችሁ።

"ወደ ውጭም አውጥቶ፦ ጌቶች ሆይ፥ እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል? ኣላቸው።
እነርሱም፦ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተ ሰዎችህ ትድናላችሁ አሉት።" (ሐዋ. 16፥ 30-31)



⇒ የእሁድ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
⇒ የአርብ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
⇒ በምጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይካፈላሉ?
⇒ ማገልገል ይፈልጋሉ?
⇒ Yeec.org App ጭነዋል?
⇒ http://www.yeec.org/ ይጎበኛሉ?

ሽማግሌዎችን ለማግኘት፦
773-886-0818 (ወ/ም ሲሳይ)
773-507-0194 (ወ/ም አያሌው)
773-910-0485 (ወ/ም ፒተር)
773-961-5332 (ወ/ም ጌቱ)
773-739-0437 (ወ/ም ሰለሞን)

**መደበኛ ፕሮግራሞች**
እሑድ 1፡30 p.m. -- 4፡30 p.m.
አርብ 7፡00 p.m. -- 9፡00 p.m.

| የቺካጎ የምስራች ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን | | Chicago Yemsrach Evangelical Church |
|---|---|---|

"እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ" ሉቃስ 2፡10




"ቸር ነውና፥ ምሕረቱ ለዘላለም ነውና እግዚአብሔርን አመስግኑ።"
(መዝ. 107፡1)

| Chicago Yemsrach Evangelical Church<br>4455 N. Seeley Avenue<br>Chicago, IL 60625 | መደበኛ ፕሮግራሞች<br>እሑድ 1፡30 p.m. -- 4፡30 p.m.<br>አርብ 7፡00 p.m. -- 9፡00 p.m. |
|---|---|
| **November 25, 2018** | **ሕዳር 9፣ 2011 ዓ.ም.** |

## የእለቱ አገልግሎት መርሃ-ግብር

| | |
|---|---|
| ጸሎት መሪ................ | እህት ሰናይት ከበደ |
| አምልኮ...................... | የቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ቡድን |
| ፕሮግራም መሪ .......... | ወንድም ጴጥሮስ መኩሪያ |
| ቃል ............. | ወንድም ጻደቀ ጴጥሮስ |
| ማጠቃለያ ................ | ፕሮግራም መሪ |

**<u>የሳምንቱ ጥቅስ</u>**

# “ምስጋና የሚገባውን እግዚአብሔርን እጠራለሁ፥ ከጠላቶቼም እድናለሁ።”

(መዝ. 18:3)

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች**

| መሪ | ቀን | አድራሻ |
|---|---|---|
| ወ/ም አያሌው አስፋው | ማክሰኞ | 5030 N. Marine Dr., Chicago, IL 60640 |
| እህት ሰናይት ከበደ | ማክሰኞ | 7200 N. Ridge Ave., Chicago IL 60660 |
| ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ | ማክሰኞ | 7526 N. Ridge Blvd., Unit #3W, Chicago IL 60645 |
| ወ/ም ረድኤቱ ካሳ | ማክሰኞ | 7252 W. Everell Ave., Chicago, IL 60631 |
| ወ/ም ሳሚ ኃብተየስ | ሰኞ | 9107 Laramie St. Skokie, IL 60077 |
| ወ/ም ዮናስ ባህሩ | ማክሰኞ | 5523 N. Kenmore Ave., Chicago, IL 60640 |
| | | |

# መልዕክተ ሰንበት

ወ/ም ረድኤቱ ካሳ

### ሃሌ ሉያ።

መዝሙር 107 የምስጋና መዝሙር ነው። ዘማሪው እግዚአብሔር ለእስራኤል ያደረገውን እየቆጠረ እዝቡ አምላካቸውን እንዲያመሰግኑ ይጋብዛል። መዝሙሩ የሚጀምረው “ሃሌ ሉያ” በሚል የሃሴት ምስጋና ነው። “ሃሌ ሉያ” የሚለው ቃል “ሃሌል” እና “ያህ” የሚሉ የሁለት ቃላት ጥምረት ሲሆን የመጀመሪያው ቃል በደስታ፣ የለገደብ፣ በሙሉ ኃይል ማመስገን የሚለውን ሃሳብ ይይዛል። ሁለተኛው ቃል “ያህ” ደግሞ “ያህዌ” የሚለውን የእግዚአብሔርን ስም የሚወክል ነው። እንግዲህ “ሃሌ ሉያ” ስንል እግዚብሔርን በደስታ፣ በሙሉ ኃይልና መለቀቅ አመስግኑ የሚል የአምልኮና የምስጋና ጥሪ የሚያስተላልፍ ቃል ነው። በመጽሐፍ ቅዱሳችን እግዚአብሔርን በዚህ መልኩ እንድናመሰግን በብዙ ስፍራዎች ተጽፎልን እናገኛለን። በተለይም ደግሞ ቃሉን በምስጋና በተሞሉት በመዝሙርና በራዕይ መጻሕፍት በ32 ቁጥሮች ውስጥ እናገኘዋለን። ከእነዚህም መካከል መዝሙር 107 አንዱ ሲሆን፤ ሲጀምር “ሃሌ ሉያ” ይላል። መዝሙሩ እግዚአብሔርን በደስታና በግለት በዝማሬ አመስግኑ በማለት ጥሪ ሲያቀርብ እግዚአብሔር ለእስራኤል ያደረገውን በማሳሰብ ነው። እኛም ዛሬ እግዚአብሔር ያደረገልንን እያሰብን ሃሌ ሉያ ማለት ይገባናል።

በመጀመሪያ መዝሙረኛው እግዚአብሔር በደስታና በግለት አመስግኑ ብሎ የሚጋብዘን እግዚአብሔር ቸርና ምህረቱ ደግሞ ብዙ የሆነ አምላክ ስለሆነ ነው። የእግዚአብሔር ቸርነት በጎነቱን፣ ለጋስነቱን ሲያሳይ፤ ምህረቱ ደግሞ ይቅር ባይነቱንና በደልን አለመቁጠሩን የሚገልጽ ነው። እግዚአብሔር በዘመናት መካከል ለእስራኤል ቸርነት አድርጓል። በተለይም በዚህ መዝሙር ውስጥ ዘማሪው እንደሚዘረዝረው የእግዚአብሔር ቸርነት እስራኤልን ከጠላቶቹ በማዳን፣ ከተበተኑበት በመሰብሰብ፣ ምሪትን በመስጠት፣ ነፍሳቸውን ከበረከቱ በማጥገብ፣ እስራታቸውን በመስበር፣ የእጃቸውን ስራ በመባረክ፣ ተፈጥሮን በማዘዝና በሌሎችም ብዙ መንገዶች ተገልጧል። ምህረቱ ደግሞ እስራኤል ከአምላካቸው ዞር ባሉ ጊዜና በመከራ ሆነው ሲጮሁ ሰምቶ ከጥፋታቸው በመመለስ፣ ሞገሱንም በላቸው በማብዛት ተገልጧል።

ወገኖቼ:- እኛም “ሃሌ ሉያ” እያልን እግዚአብሔርን በታላቅ ደስታና በግለት ማመስገን ይገባናል። በተለይም በዚህ በምንኖርበት አገር “የምስጋና ቀን” ሲከበር እኛ በተለየ መንፈስ በሕይወታችን የተገለጸውን የእግዚአብሔርን ቸርነትና ምህረት እያሰብን ገደብ በሌለው ምስጋና በአምላካችን ፊት መቅረብ አለብን። እግዚአብሔር ቸርነቱን በሕይወታችን አብዝቷል። ለነፍሳችን የተጠመደውን የዲያቢሎስን ወጥመድ ሰብሮ ነጻ አውጥቶናል። ጨለማችንን ገፎ ወደ ራሱ ብርሃን አምጥቶናል። ሙታን ለነበርነው ሕይወትን ሰጥቶናል። በክፉው ፈቃድ ስንመላለስ የነበርነውን ልጆቹ አድርጎናል። የእጆቻችን ስራ ባርኮልን ምጋቦቱን አትረፍርፎልናል። ደግሞም ምህረቱ ገኖልን የፍርዳችንን የሞት እዳ በልጁ ላይ አድርጎ በሕይወት ኑሩ ብሎናል። እለት እለትም ምህረቱን በላችን አብዝቶ በፊቱ የምንቀርብበትን ጸጋ አብዝቶልናል። ሃሌ ሉያ።